እኔና አንቺ… ፫ (ወለላዬ ከስዊድን)

ትዳርና ስደት

በሕዝብ ተጋርደን ባ’ገር ተከልለን
ለካስ እኔና አንቺ ብዙም ዕውቀት የለን።
እኔን ስመረምር አንቺን እዚህ ሳይሽ
እኔም ያን አይደለሁ አንቺም ያቺ አይደለሽ።
እንዲህ ካደረገን ስደት አሸንፎ
ጭራሽ ከሚለየን ኑሮአችንን ገፎ
ሥርግ ባንደግስም ባይረጭ አበባ
በአዲስ ትውውቅ ድጋሚ እንጋባ።